# ይድረስ ለትግራይ ህዝብ !!!





















… የቅድመ ታሪክ ሐዋርያ፣
የንግሥተ - ሳባ ዝርያ፤
… የጥንት የጠዋቱ አምሳል፣
የእማማ ኢትዮጵያ አካል፤
የማኅሌታይ ያሬድ ዜማ - የግዕዝ፥ የዕዝል፥ የአራራይ …
«የፑሽኪን ቅኔ» መሠረት - ለሩስያ …ለዓለም ሲሳይ፤
የድጓ፡ የፆመ - ድጓ … የብራና መፍለቂያ፣
የደብር፥ የገዳማት … የሊቀ ሊቃውንቱ ማፍሪያ፣
የአክሱም ጽዮን ጉልላት - የፈጣሪ ቃል ማደሪያ፣
የጥንተ - ሥልጣኔ ፈር ቀዳጅ
የአክሱም ሐውልቶች መቆሚያ፣
ደማቅ ሥም አጎናጻፊ ለእምዬ እናት ኢትዮጵያ፤

**ይድረስ ለትግራይ ሕዝብ !!!**
መሰሪ ከሚዘረጋብህ ወጥመድ፣
ጠልፎ ከሚጥልህ ገመድ፤
እኩይ ከሚተበትብብህ መተት፣
ከሚያደነዝዝ ክፉ ልክፍት፤
እባብ ከሚረጭብህ መርዝ፣
ለልጅ - ልጅህ ከሚተርፍ መዘዝ፤
ሸፍጠኛ ከሚደግስልህ ግብዣ፣
በመርዝ የተለወሰ ጉርሻ፤
አደራ እጅህ እንዳይዘረጋ፣
ከቶ ላፍታም እንዳትዘናጋ !!!

… የድል ብሥራት ባለ ዕድል፣
የነፃነት ክቡር ጸበል፤
የጥቁር ዘር መኩሪያ አምባ፣
የአድዋ ምድር ባለ ካባ፤
በላቡ ጥሪት ለፍቶ አዳሪ፣
በማተቡ ጸንቶ ኗሪ።

**ይድረስ ለትግራዩ ለወገኔ !!!**
ተፋቅረን እንዳንኖር አንተና እኔ፤
መሰሪ ጉድጓድ እንደሚምስ እንወቅ፣
እጅ - ለእጅ ተያይዘን እንጠንቀቅ !!!









... ባያት ቅድማያቶችህ ደም አጥንት፣
ባባት በእናቶችህ ላብ ጥሪት፤
ለዘመናት የተገነባ ታሪክህን፣
በጥበብ የተካነ ባህልህን፤
በእምነት የጠበቀ ማተብህን ....
ሊነጥቅህ ከሚያንሰራራ፣
ካኮበኮበ ጆፌ አሞራ፣
አቤቱ ! ተጠንቀቅ አደራ !!!

ይድረስ ለጭቁኑ የትግራይ ሕዝብ !!!
ከላይም ከታችም እንዳትነደፍ በመርዘኛ እባብ !

... ትናንትም ዛሬም በሥምህ እየነገደ፣
በሐሰት ፕሮፓጋንዳ እየቀፈደደ፤
ሥምህን እየጠራ እየማለ፣
ሕዝባዊ ወያኔ ሃርነት እያለ ...
እሱ ጮማ ሲቆርጥ እያገላበጠ፣
ሲተርፈው «ማሌቹያ ባንክ» እያስቀመጠ፤
ትግራይን አለማለሁ እያለ፣
ባፌ - ጮሌ ካድሬዎቹ እያማለለ፣
ላም አለኝ በሰማይ እያስባለ፤
ጥረህ ግረህ ሳይሞላልህ አንጀትህን አስረህ ለምትኖረው፣
ከማማቀቅ በቀር ምን ፈየደ እስኪ ቆም ብለህ መርምረው፤

«አክሱም ለወላይታ ምኑ ነው .......»
«ሶፍ ዑመር ለትግራይ ባዕድ ነው ........»
እያለ ከንቱ ሲያቅራራ፣
ከወገንህ ሊለይህ በሴራ፤
ዜማ አልባ ጩኸቱን የእልቂት መዝሙር እየዘመረ፣
«መ0ት» የሚመኝልህን ጆሮህን እያደነቆረ፤
እንደ «ጆከር - አኪር» እየሳበ ሥምህን ለማስፈራሪያ፣
«ኢንተርሃምዌይ»ን እየጠቀሰ
መተራረድን ሲመኝ ለኢትዮጵያ፤
ልብ ብለህ መርምረው፣
እስከዛሬም እንዳደረገኸው፣
ባስተዋይነትህ እንደታገስከው፣
አጎንብሰህ አሳልፈው፣
ደግሞም ታገል ተፋረደው።

ይድረስ ለአሉላ ልጅ ለሃቀኛው !!!
ሃገርህ ስትጠቃ ለማትተኛው፤
የጥንተ - ዘር ... ኢትዮጵያዊ፣
ለሃገሩ ክብር ቀናዒ፤
ልጆችህን ገብረህ ያስጠበቅኸውን ክብርህን፣
በጓዳ እያስነጠቀ ባደባባይ ያዋረደህን፣
ላፍታም እንዳትዘነጋው የባድመ ደመኛህን፤
ውጉዝ ይሁን ከመ - አርዮስ፣
የደረስክበት ላይደርስ !

... የስልጣን ጥሙን ሊያረካ፣
ድብቅ ፍላጎቱን ሊያሳካ፤
ስንት ልጆችህን እንዳረደ፣
ስንቱን ወህኒ እንደቀፈደደ፣
ስንቱንስ ከሃገር እንዳሳደደ ...
ልብ ብለህ መርምረው፣
ምሣሌው ነግ - በኔ ነው !!!

ይድረስ ለትግራይ ልጅ ለሃገሬ !!!
በታሪክ ፈተና ውስጥ ብትሆንም ዛሬ፤
በአርቆ አስተዋይነትህ፣
በሁሉን ችሎ ማደርህ ...
እንደምትወጣው ይሄን የጊዜ ቱማታ፣
ተጠራጥሬም አላውቅ ላፍታ፤
ተከባብረን ተደጋግፈን፣
የመከራን ጊዜ አልፈን፤
እጅ - ለእጅ ተያይዘን ለምንኖርባት ኢትዮጵያ፣
ለዚያች ዕለት ዳግም ያብቃን አሜን ! ሃሌሉያ !!!

ጌታቸው አበራ
የካቲት - 1998 (፲፱፻፺፰)